# ለቀድሞ የኢሕአፓ አባላት
# መልዕክተ ተጠሪ

የተከበራችሁ ነባርና ጥሪ የተደረገላችሁ የቀድሞ የኢሕአፓ አባላት ሆይ!

ከምስረታው ጀምሮ የዓላማው አገልጋዮች የሆኑት ፓርቲውን በጽኑ አቆይተው ለዚህ ጥሪ እንዳበቁት ሁሉ ለቀጣዩም ትውልድ እንዲያስተላልፉልን በኢሕአፓ ዘንድ ስለ ተፈጸመው ነገር ጥቂቶች ታሪኩን ለማዘጋጀት ቢሞክሩም እኔ ደግሞ ስለ ተማርኩት፣ ስለ አሳለፍኩት፣ ስለ አየሁት፣ ስለ ሰማሁት፣ ስለ አነበብኩት በመጠኑ ልግለጽላችሁና ጉባዔው ስኬታማ ይሆንልን ዘንድ እንድንሠራ ይህንን አጭር መልእክቴን ላስተላልፍላችሁ መልካም ሆኖ ታየኝ።

በ1966 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ከዳር እስከ ዳር የተቀጣጠለው የሕዝብ ትግልና ዓመጽ ለዘመናት በፊውዳሉ ሲረገጥና ሲበዘበዝ የነበረው ሕዝብና አርሶ አደሩ እንደሥርዓቱ ከተጣለበት የመረገጥ፣ የመበዝበዝ፣ ሰጥ ለጥ ብሎ የመገዛት ግዴታ ባሻገር የጊዜው ባለሀብቶች ተጨማሪ የረሀብ፣ የበሽታ፣ የድንቁርና፣ የስደት ገፈት ቀማሽ እያደረጉት በመምጣታቸው የተነሳ ያለው ብቸኛ አማራጭ ሥርዓቱን ሙሉ በሙሉ መንግሎ መጣል በመሆኑ በቃኝ፣ እምቢኝ፣ አልገዛም ብሎ የድል ባለቤትነቱን እስኪያረጋግጥ የተንቀሳቀሰበት፣ የተዋደቀበት፣ የተጋደለበት አብዮት ነበር። በእርግጥም በድል አድራጊነት የፊውዳሉን ሥርዓት ገርስሦ ጣለው። የድሉን ፍሬ ግን አለሁልህ ባይ ቀማው።

በወቅቱ ዘጠና ከመቶው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮው በግብርና ላይ የተመሠረተ ሲሆን አብዛኛውን መከራና ግፍ ተቀባዩ አርሶ አደሩ ክፍል በመሆኑ መሪ የነበረው የሕዝብ መፈክር «መሬት ለአራሹ» መሆኑ ውቅታዊነቱ አጠያያቂና አነጋጋሪ አልነበረም። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ያለጥርጥር ሥር ነቀል የሆነ ለውጥ በአገሪቷ ላይ ማምጣት፣ ማስፈን ያስፈልግ ነበር።

የሕዝብን ብሶት፣ የሕዝብን ጥያቄ፣ የሕዝብን ችግር ሊፈታ የሚችል በማንኛውም ጊዜ ሕዝቡ ራሱ ብቻ በመሆኑ ለስኬታማነቱም አብረው የሚነሱ ጥያቄዎች ዋነኛና ቁልፍ ነበሩ።

- የዲሞክራሲ መብቶች መከበር፣
- የሕዝቡ የራሱ የሆነ መንግሥት መመስረት፣
- የብሔር ብሔረሰቦችን መብት ማክበር፣
- ሃይማኖትና መንግሥትን መነጠል፣
- የፆታ እኩልነትን ማስፈን፣ . . . ወዘተ.

ከዚህም ጋር ተያይዞ የአገሪቷንና የሕዝቡን የወደፊት ዕድል ቀና ለማድረግና አገሪቱ ወደ ዕድገት የምታመራበትን ጎዳና በሚቀይሱና በሚነድፉ ፕሮግራምና ፖሊሲ የተገኘውን ድል የሕዝቡ ለማድረግ የተዘጋጀና የተደራጀ የፖለቲካ ድርጅት በወቅቱ ባለመኖሩ የሕዝቡን የዳር እዳር እንቅስቃሴ ተገን በማድረግ የታጠቀው የወታደር ክፍል ጥያቄዎቹን የሕዝቡን ስሜት ለመቆጣጠሪያ በመጠቀም ሥልጣኑን ሊቆናጠጥ ችሏል።

የወታደራዊው አገዛዝ ገና ሥልጣኑን እንደያዘ የመጀመሪያው እርምጃ የሕዝቡን መብት ማፈንና መገደብ መጀመር በመሆኑ በዚህ ጊዜ ነበር በየአቅጣጫው በተማሪው፣ በሠራተኛው ክፍል፣ በየገጠሩ ወዘተ. ተቃውሞ እየገጠመው የመጣው። ወታደራዊው አገዛዝን በሕዝብ መንግሥት

ለመተካት፣ ላልተመለሰው የሕዝብ ጥያቄ አማራጩ ያልበረደውን የሕዝብና የልጆቹን የትግል ስሜት ይዞ መጓዝና ለድል ማብቃት በወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳይ በመሆኑ በጊዜው በህቡዕ በመንቀሳቀስ ላይ የነበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ድምጹን በማሰማት እራሱን ይፋ ያደረገው።

ኢሕአፓ በወቅቱ ይዞ የተነሳው የራሱን መፈክር ሳይሆን የሕዝብን ነበር። ለዚህም ነው በአጭር ጊዜ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትን ሊያገኝ የቻለው።

- «መሬት ለአራሹ» ዋናው የአርሶ አደሩ ጥያቄ ሲሆን ለብዙ ዘመናት ወጣት ተማሪዎች ሲያስተጋቡትና ሲሰዉለት የነበረ መፈክር ኢሕአፓ መሪ መፈክሩ አድርጐታል፣
- የዲሞክራሲ መብት መከበር የሕዝብ ጥያቄ ነበር፣ ኢሕአፓም በርግጥ ያለገደብ አስተጋብቶታል፣
- የሕዝብ መንግሥት መመሥረት የራሱ የሕዝቡ ጥያቄ ነበር፣ «ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት አሁኑኑ»ን የወቅቱ መፈክር በማድረግ ኢሕአፓም ታግሎ  አታግሎበታል፣
- የብሔር ብሔረሰቦች መብት መከበር አንገብጋቢው ጥያቄ ነበር፣ በመርህ ደረጃና በወቅቱ በነበረው ሶሻሊስታዊ ርዕዮት መሠረት እስከመገንጠል ታክሎበታል፣ ሌላም፣ ሌላም

ወቅቱ ዓለም በሁለት ጎራ የተከፈለችበት ሲሆን ትግሉ የመደብ ትግል በመሆኑ ስለ እኩልነት፣ ጨቋኝና ተጨቋኝ፣ ገዥና ተገዥ፣ በዝባዥና ተበዝባዥ ቃላቶችና ትንታኔዎች በከፍተኛ ደረጃ የሚወሱበትና ለዚህም ብቸኛ አማራጭ ተደርጎ የነበረው ብዝበዛንና ጭቆናን አጥፍቶ በእኩልነት ላይ የተመሠረተች ኢትዮጵያን መመሥረት ነበር። በመሆኑም ሶሻሊዝም ጊዜ የፈጠረው የወቅቱ ርዕዮተ ዓለም ስለነበር የኢሕአፓ የፖለቲካ መመሪያው ነበር። ተያይዞም ላብ አደራዊ አምባገነንነት ተስተጋብቷል።

ኢሕአፓ በወቅቱ የሕዝቡን ጥያቄ መሪ መፈክሩ አድርጎ ሲነሳ የድርጅቱ ዓላማ ዓላማችን፣ የሕዝብ ብሶት ብሶታችን፣ አድርገን ድርጅቱን የተቀላቀልን ዛሬ ላይ ሆነን ስናየው በልጅነትና በወጣትነት ስሜት በመገፋፋት፣ ባለማስተዋል ሳይሆን ትልቁ ግባችንና ትግላችን

- ለሕዝባዊ መንግሥትና ለሀገር አንድነት ፡
- ለኢትዮጵያ ሕዝብ እኩልነት፣ አንድነትና ነፃነት ፡
- ለብሔር ብሔረሰቦች መብት መከበር ፡
- ገደብ ለሌለው የዲሞክራሲ መብት መከበር ፡  ወዘተ ነበር። ነውም።

ኢትዮጵያ ሀገራችንን ወደ ዘለቄታዊ ዕድገት፤ ሕዝባችንን ለጥሩ ሕይወት፤ ረሃብ፣ በሽታ፣ ድህነት፣ ድንቁርናን ለማጥፋት፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በአንድነት ያለአድልዎ በጋራ የሚኖርባት፣ የሚማርባት፣ የሚያድግባት፣ ሕጻናት በእንክብካቤ ተይዘው ቦርቀው የሚያድጉባት ሀገር ለመገንባት፤ ሃይማኖት፣ ፆታ፣ ዕድሜ፣ ብሔር፣ ዘር፣ ክልል ሳንለይ በአንድ ላይ የተነሳነውና የተጋደልነው ለክቡር ዓላማ፣ ለተቀደሰ ተግባር በመሆኑ ልንኮራበት፣ አሁንም ሆነ ወደፊት ልንተርከው የሚገባን ተጋድሏችን ነው።

በሙሉ የሀገር ፍቅር ስሜት፣ በከፍተኛ ወኔና ቆራጥነት ለትግሉ ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡ ወንድሞቻችን፣ እህቶቻችን፣ እናቶቻችን፣ አባቶቻችን፣ ሕፃናት ሁሌም የምናስታውስበት፣ እኛም ቀናችን ስላልተቆረጠ አልሞትንም ብለን የምንዋሽ ከአረመኔውና ከፋሽስቱ ወታደራዊ መንግሥት ጋር በአደረግነው ተጋድሎና በተከፈለው መስዋዕትነት የድሉን ፍሬ እስከዛሬ ባናይም የጥንት

የአባቶቻችን ወኔ፣ ቆራጥነት የተከተልንበት፤ ለሀገር፣ ለሕዝብና ለድርጅት ያለንን ታማኝነት አሳይተን ያለፍንበት አኩሪ ታሪካችን መሆኑን የምንመሰክርበት እንጂ አንገት የምንደፋበት አይደለም።

ለምን ለድል አልበቃንም? ለምንስ ትግሉ ተዳከመ? ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ። ዋናው መሠረታዊ ጉዳይ ግን ለሀገር አንድነት፣ ለሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት፣ ለነፃነት፣ ለሰንደቅ ዓላማችን እንጂ ሀገር ለመሸጥና በሀገር ጉዳይ ለመሞዳሞድ፣ ለንዋይ ፍለጋ፣ ለባንዳነት የተሰልፍን አልነበርንም። አሁንም አይደለንም።

እኛ የኢሕአፓና የሕዝብ ልጆች ዋናው ተቀዳሚ ዓላማችን ለሀገራችንና ለሕዝባችን ያለን ብርሃናዊ ራዕይ ስለነበር ትምህርት ከድል በሁዋላ ብለን ትምህርታችንን በመተው፤ ቤተሰብ፣ ወንድም፣ እህት፣ እናት፣ አባት፣ ልጅ ከሀገራችን ሕዝብ ሳንለይ ያም ቤቴ ነው ብለን ፋኖ ተሰማራ ያልንና በረሃ ለተጋድሎ የገባን፤ እጅግ በጣም የተፋፋመውን የሕዝብ ትግል ለድል ከማብቃት በስተቀር ሌላ ያልታየን ብዙ ነበርን። ያም ይባል ይህ በፋሽስቱ ወታደራዊ መንግስት በኩል የነበረውን የጦርና የኃይል ሚዛን አለማመዛዘንና ከፋሽስቱ ጋር የተሰልፉትንና ያጠቁንን ውስጥ አዋቂ ባንዳዎች መናቅ፣ ለፋሽስታዊው መንግስት የጅምላ ጭፍጨፋ አመቺ ሁኔታ በመፍጠራቸው ዳር እስከዳር ለተሰነዘረው ፀረ-ኢሕአፓ ዘመቻ ሂላማ በመሆን ልንመታና ልንዳከም በቅተናል።

ደርግ ኢትዮጵያን እንደአሻው ሊገዛና ሕዝቡንም እንደፈለገው ሊያሰቃይ፣ የሀገሪቷን ሀብት ሊመዘብር የሚችለው ሕዝቡን ፀጥ ለጥ አድርጎ ሊገዛ ሲችል፣ የውሸት ዲስኩሩንና ልፈፋውን በግድ ሕዝብ እንዲቀበለው ማድረግ ሲችል ብቻ ነበር። ስኬቱንም ተግባራዊ ለማድረግ በአለው የጭካኔ በትር ሕዝቡን መምታት ማለት ኢሕአፓን ማጥፋት በመሆኑ ለዕድሜው መራዘም ሲል ያለ የሌለ ኃይሉን በኢሕአፓና በሕዝብ ላይ አሳረፈ። ኢትዮጵያ በልጆቿ ተከብራና አድጋ የማየት ፍላጎት የሌላቸው ባዕዳን ኃይሎችና የውስጥ ባንዳዎች ለፋሽስታዊው አገዛዝ ቀጣይነት ያደረጉት እገዛ በተጨማሪ ኢሕአፓን አዳከመው።

ደርግና ጀሌዎቹ የሰው ልጅ ይፈጽመዋል ተብሎ የማይገመት፣ ለማመን የሚከብድ ግና የተደረገ ጭፍጨፋና ስቃይ በጅምላ አካሄዱ። በባህላችን፣ በሃይማኖታችን፣ በታሪካችን የሌለና ታይቶ የማይታወቅ ትውልድ ጭፍጨፋ በሀገረቷ ላይ ሲሰፍን ደርግ ዋናው ግቡ የአገዛዝ ዕድሜውን ማራዘም ነበር።

- ልጅን ቤቱ በራፍ ገድሎና ጥሎ ወላጅ እያየ እንባውን እንዲውጥ ማስጠንቀቅ ፡
- እናት አባት አቁሞ እፊታቸው ልጃቸውን መግደል ፡
- እርጉዝ እናት መግደል (ዳሮ ነጋሽ ለአብነት) ፡
- ታዳጊ ሕፃን በአዋጅ መግደል (ባቢሌ ኃ/ሥላሴ ለአብነት) ፡
- እኔ ልግደል እኔ ፋክክር የታየበት ፡
- ቀይ ሽብር ለዘለዓለም ይኑር! መፈክር የተወረደበት ወዘተ. ወዘተ.

እልቂቱና ጭፍጨፋው ከዚህ ባሻገር በፖለቲካው ላይ ብቻ ያነጣጠረ አልነበረም። በቂም በቀል፣ በቅናት መንፈስ፣ ንብረትን ለመዝረፍ፣ ሚስትንና የደረሱ ወጣት ሴት እህቶቻችንን በማስገደድ ለማግባጥ ወዘተ. ከፖለቲካው ሌላ ያለቀው ዜጋ እራሱ ቀላል አልነበረም።

በየከተሞችና በገጠሩ በነበሩት የደርግ እስር ቤቶች የነበርን እያንዳንዳችን ያየነውንና የነበረውን ብንተርከው ምን ዓይነት የጭካኔ ዘመን ነበር ያሰኛል። ሕይወታቸውን የሰዉት የኢሕአፓ ልጆችም

የመጨረሻው ድምፃቸው «ኢሕአፓ ያቸንፋል»፡ «የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል» ነበር። ለዕርድ የቀረቡትም መዝሙራቸው/መፈክራቸው «የትግሉ ነው ሕይወቴ» ነበር። በተግባርም አድርገውታል። በወደቁት ጓዶች ፋና ተጉዘዋል።

ድርጅቱንና ትግሉን ላለማጨናገፍ ሲሉ እራሳቸውን ያጠፉ የኢሕአፓ ቤት ይቁጠራቸው። ከፎቅ የተወረወሩ፡ ፈጣን ገዳይ መድሐኒት የዋጡ፡ የቴዎድሮስን አርዓያ የተከተሉ፡ አጥፍቶ መጥፋት የፈፀሙ ወዘተ. እነሱ ተሰውተው እኛ ትግሉን እንድንቀጥል ነው። እነሱ ተሰውተው ለማያጠራጥር ድሉ እኛ እንድንበቃ ነው። እነሱ ሞተው ኢሕአፓና ሕዝብ ለድል እንዲበቁ ነው። እነሱ ሞተው ኢትዮጵያ ሀገራችን በድል፡ በክብር፡ በነፃነት የሕዝብ ሀገር እንድትሆን ነው። እነሱ ሞተው አረንጓዴ-ቢጫ-ቀይ ሰንደቃችን ከደቡብ-ሰሜን፡ ከምዕራብ-ምሥራቅ እንዲውለበለብ ነው። እነሱ ሞተው ቀጣዩ ትውልድ ብሩሕ ተስፋ እንዲያይ ነው። ነበር።

ዘግናኝና አስከፊ ቢተረክ፡ ቢፃፍ ሊታመን በማይችል መልኩ የተደረገው የደርግ የአንድ ትውልድ ማጥፋት ዘመቻ ሀገሪቷ እጅግ ልትትካው የማትችለውን ብርቅዬዎችን በፖለቲካው፡ በትምህርቱ በአጠቃላይ በሁሉም መስክ በማሳጣት ኢትዮጵያን የገደለና ለድህነቷ ከፍተኛ አስተዋጽዎ ያደረገ ነው። ደርግ በአደረሰው አረመኔያዊ ጭፍጨፋና በደረሰብን ስነ ልቦናዊ ተፅዕኖ እርስ በርስ አለመተማመን፡ ወንድም ከወንድሙ፡ ከእህቱ፡ ከእናቱ፡ ከአባቱ፡ ከዘመዱ፡ ከጓደኛው፡ ወዘተ አለመተማመንና እርስ በርስ ጥርጣሬ ዓለም ውስጥ ተዘፈቅን። በብቸኝነት ዓለም ተዋጥን። እናም ወንድሞቻችን፡ እህቶቻችን በትግሉ ተሰውተው እኛ ፈራን። ውስጣችን እየተቃጠለ ትግሉን ሸሸን። አልቅሰን አልወጣልን ዕድሜ ልክ አለቀስን። በአንድ አፍ እንናገር፡ በአንድ ጆሮ እንሰማ፡ በአንድ ዓይን እናይ፡ የነበርን የኢሕአፓና የሕዝብ ልጆች ዲዳነት፡ ደንቆሮነትና ጨለማ ወረሱን። በትግሉ ሜዳ የተሰዉትን ወንድሞቼን፡ እህቶቼን ዘነጋኋቸው። እኔም ጥይት ስቶኝ፡ እኔም አልታይ ብዬ ነው በሕይወት ያለሁት። ቆሜ እሄዳለሁ፡ እተነፍሳለሁ እንጂ መቃብር ያለኸው ወንድሜ፡ መቃብር ያለሽው እህቴ ኑዛዜአችሁን በልቼ፡ ቃል ኪዳኔን አፍርሼ፡ አርማችሁን ጥዬ እስከተገኘሁ አልሞትሁም ብዬ አልዋሽም። እኔም ሞቻለሁ።

እኛ የኢሕአፓ ልጆች ከዚህ ሁሉ አረሜናዊ ጭፍጨፋ የተረፍን ምንጊዜም ውስጣችን ያለና የፀና መንፈስ አለ። ይኸውም ኢትዮጵያ ሀገራችንን እንወዳለን፡ ሕዝባችንን እንወዳለን፡ ሰንደቃችንን እናከብራለን፡ ሃይማኖታችንን እናከብራለን፡ በባህላችን እንኮራለን። በደርግ አገዛዝም ይሁን አሁንም በወያኔ የሀገራችን ሁኔታ ውስጣችንን የሚበላን፡ የሚቆጠቁጠን ነን። ይህ ደግሞ በተዓምር ሳይሆን ከአሳለፍነው የልጅነትና የወጣትነት ዕድሜአችን ጀምሮ ከተቀረፀው የሀገር ፍቅር ስሜት በተጨማሪ በአሳለፍነው የትግል ተመክሮ የኢሕአፓም አስተዋጽዎ እንዳለው ልንክድ አንችልም። ብዙ የኢሕአፓ ልጆች ዛሬም ከወያኔ ጋር በሚደረገው ትግልና ትንቅንቅ በተለያዩ የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽዎ እያደረጉ መገኘታቸው ለዚህ ጉልህ ምስክር ነው።

ወደ እራሳችን የግል ሕይወት ሁኔታዎችን ስንመለከት ከደርግ ተከታታይ አፈናና ማሳደድ እራሳችንን ለመከላከል ወደ ስደት፡ ትምህርት፡ ሥራ መስክ፡ ትዳር ወዘተ. በመግባት አብዛኛው የኢሕአፓ ልጆች ስኬታማ ውጤት ማስመዝገባቸው፡ በማኅበራዊ ኑሮና በባህሪም አሁንም በየአካባቢያቸው ሕብረተሰቡን አክብረውና ተከብረው ያሉ ለመሆናቸው እራሳችን ለራሳችን ምስክር ነን።

ኢሕአፓን የራሱ ስህተቶችና ድክመቶች ካደረሱበት ችግሮች ሌላ የወታደራዊው ደርግና ተባባሪ ቡድኖች የተቀነባበረ ሸብርና ጭፍጨፋ፡ የአካባቢና የሌሎች ሀገሮች ፀረ-ኢትዮጵያ አቀዋሞችና

እንቅስቃሴዎች፡ እንዲሁም የጠባብ ብሔረተኛ ድርጅቶች ሻጥርና ተደጋጋሚ ጦርነቶች፡ እስካሁንም ያልቆሙ የማጥፋት ሙከራዎች ያለጥርጥር ጎድተውታል። መላልሰው አዳክመውታል።

ኢሕአፓ በአሳለፈው የትግል ተመክሮ ከስህተት የፀዳ ነበር፡ ነውም ብሎ መናገር ራሱን የቻለ ስህተት ነው። ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ያለው ራዕይና ጽናት እንደተጠበቀ በሂደት ላይ ስህተት ተሰርቷል። ይህ ደግሞ ምንጊዜም የሚነሳና በስህተትነቱ የታመነበት ለትምህርት ሰጪነቱ በታሪክ መዝገብ የሚሰፍርና  የሚቀበለው እንደሆነ ጥርጣሬ አይኖረንም። ደርግ፡ ወያኔና ሌሎች የኢትዮጵያና የኢሕአፓ ጠላቶች ከሚያናፍሱትና ከሚያራግቡት ውሉ የጠፋ የወሬ ዘመቻ ባሻገር እኛ ነባርም፡ የቀድሞም የኢሕአፓ አባላት ኢሕአፓ አደረጋቸው የምንላቸው ስህተቶች ይኖራሉ። አሉም።

ስህተት ነበር አልነበርም ተብሎ ለክርክርና ለውይይት ሊቀርቡ የሚችሉ ጉዳዮች ብዙ አሉ። ለአብነት ያህል ለመጥቀስም ፡

- የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም ጉዳይ ፡
- የብሔር ብሔረሰቦችን መብት እስከመገንጠል መቀበል ፡
- የኤርትራ ጥያቄ ፡
- የ1969 ዓ.ም. የሶማሊያ ወረራ በኢትዮጵያ ላይ ፡
- የከተማው ትጥቅ ትግል ፡
- የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢሕአሠ) ጉዳይ ፡
- በፓርቲው ውስጥ ስለተፈጠረው አንጃ ፡ ወዘተ. እና ሌሎችም ሊነሱ ይችላሉ።

በጊዜው በነበረን ብስለትና አሁን ደግሞ ዕድሜ እያስተማረን ብዙ እያገናዘብን ስንመጣ መሆን አልነበረበትም ከምንላቸው ባሻገር ያለ ዝርዝር ምክንያትና በቂ መረጃ ድርጅቱን ተጠያቂ ለማድረግ የምንሠነዝራቸው ሀሳቦችም እንዳሉ መገንዘብ ይኖርብናል።

ዋናው መታየት ያለበት ቁም ነገር በድርጅቱ የአካሄድና የታክቲክ ስህተቶች ናቸው የተፈፀሙት? ወይስ የዓላማ? የሚለው ነው። በዓላማው ጥንትም ለኢትዮጵያ ክብርና ለሕዝብ አንድነት፡ ነፃነት፡ መብትና እኩልነት የቆመ አሁንም በዚህ ዓላማው የፀና ድርጅት ነው። ለማንም የባዕድ ኃይል ሆነ የውስጥ አምባገነን ያላጎበደደ ቀዳሚ ዓላማው ወቅቱ የሚፈጥራቸውን የሕዝብ ጥያቄ የሚያነሳ ፓርቲ ነው። ለዚህም ነው ደርግም የሕዝብ አይደለምና የኢሕአፓ ጠላት፡ ወያኔም የሕዝብ አይደለምና የኢሕአፓ ጠላት የሆኑት።

በተለያዩ ብዙ መድረኮች አሉ የተባሉ ስህተቶች ውይይት ተደርጎባቸዋል። አሁንም፡ ወደፊትም ይደረግባቸዋል። ስህተት አስተማሪ ነውና ከዚያ ብዙ ትምህርት ተቀስሟል። ወደፊትም ይቀስማል። እንኳን ለኢሕአፓ ለሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ቅንነቱ ከአለ ብዙ ይቀሰማል። አሁንም እየተደረጉ አሉ የሚባሉ ስህተቶች ከነባር አባላት ጋር መድረኩን በመጋራት ሊስተካከሉ የሚገባቸው እየተስተካከሉ በድርጅታችን ውስጥ ገብተን ለሌላ የሥራ መስክ መቀጠሪያ ሪዚዩሜ ሊሆን የማይችለውን የትግል ልምዳችንን አሁንም ለኢሕአፓና ለሕዝብ እናበርክተው እላለሁ።

ከደርግ አፈናና ጭፍጨፋ በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች በፓርቲው ውስጥ ተሳትፈን ትግሉን ባንገፋበትም ኢሕአፓ ከሕዝቡ እንዳይርቅ፡ የኢሕአፓንና የተሰውለትን ልጆቹን አርማ እንግበው እስከዛሬ ኢሕአፓን ያቆዩትን፡ ስለ ሕዝብ መብትና የስልጣን ባለቤትነት ሲነሳ ያለ ኢሕአፓ የማይታያቸውን አምባገነን ገዥዎች እስከዛሬ እንደባነኑ እንዲጓዙ፡ እንዳይደላደሉ ፋታ ያሳጡትን

አባላቱን ምስጋና ይግባቸውና ዛሬ ኢሕአፓ ጥሪ ያደርግላችኋል ሲሉን የሕዝብ ጥሪ፡ በትግሉ የተሰዉ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ጥሪ፡ የደም ጥሪ መሆኑን እንድንገነዘብ ይገባናል።

ከደርግ ውድቀት በቀጣይነት የጥፋት በትሩን ይዞ እጅግ በፈጠነ ሁኔታ ሀገርና ሕዝብ ሊያጠፋ የተተካው ወያኔ ብዙ ተብሎለታል። በዚህ መልዕክቴ ስለ ወያኔ ምንነት ለመድገም አይደለም። ቢደገም አይደለም ቢደጋገም አሁንም አንገብጋቢው ጉዳይ ኢትዮጵያ ሀገራችን ያለችበት ሁኔታ ነው። ሀገርና ሕዝብ በአደጋ ላይ ናቸው። ስለቱ በተቀባበል ጥይት ላይ ናቸው። የጥፋት ፈንጂ ተጠምዶላቸዋል።

በፀረ-ኢትዮጵያዊነት ባህሪው ሀገር ለማፈራረስ፡ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር እንዳትኖር፡ አንዱን ብሔር ከሌላው ለማጋጨት፡ አንዱን ሃይማኖት በሌላው ላይ ለማነሳሳት ዕቅዱና ዓላማው አድርጎ የተነሳው ወያኔ በትረ መንግስቱን ከመጨበጡም በፊት ከጨበጠም በኃላ ኢሕአፓ በከፍተኛ ደረጃ ተቃውሞውንና ድምፁን አስተጋብቷል። ገና ከጅምሩም ዳግም ጠላቱን ኢሕአፓ ያደረገው ወያኔ የጭካኔ በትሩን በኢሕአፓ ላይ በማዞር ያደረሰው ጥፋት የሚዘነጋ አይደለም። ሆኖም ትግላችን የሕዝብ ነውና፡ ትግላችን ከሕዝብ ጋር ነውና ላጥፋህ ቢሉት የማይጠፋ ኃይል ሕዝብ ነው።

ኢሕአፓ ጥንትም አሁንም በሕዝቡ ስሜት ውስጥ እንዳለ ነው። እናቶች፡ አባቶች፡ ላብ አደሩ፡ አርሱ አደሩ፡ ሠራተኛው ወዘተ. በአብዛኛው በጥሩ መልኩ ያውቁታል። ይህንን ደግሞ ከእኛ በላይ ወያኔ ጠንቅቆ ስለሚረዳው ኢሕአፓ ቀዳዳ አገኘ ማለት ከማይወጣው ማጥ የመግቢያ ጊዜው ስለሚቃረብ በሚያገኘው አጋጣሚ ሁሉ ከፀረ-ኢሕአፓ ዘመቻው ለሰከንድም አይዘናጋም።

ከላይ እንደተገለጸው ኢትዮጵያ ሀገራችንን በመውደዳችን፡ የሕዝቡን ችግር ችግራችን፡ ብሶቱ ብሶታችን የነበርን ሁሉ የኢሕአአፓ አባላት በተለያየ መነገድ አሁንም ፀረ-ወያኔ ትግሉን በአብዛኛው ተያይዘውታል። በተለያየ ፀረ-ወያኔ ድርጅቶች ውስጥ አሁንም በከፍተኛ እንቅስቃሴ ላይ ያሉት የኢሕአፓ ልጆች የነበሩ ናቸው። ለዚህም የተለያየ ምክንያት ሊኖረው ቢችልም አሁንም ድርጅቱ በሀገር ውስጥ ጐልቶ ቢታይ ከደርግ ባልተናነሰ ወያኔ የጥፋት እጁን እንደሚዘረጋ ለአፍታ ሳንዘነጋ በረቀቀና በሰከነ መንፈስ ትግሉን ልናግዝ ይገባናል። በተለያዩ የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች ተገንነት ትግልን መቀጠሉ ለጋራ ዓላማ እስከሆነ ድረስ አዎንታዊ ገጽታ ቢኖረውም በቤታችን ገብተን መሰባሰቡ ደግሞ ጓዳ ጉድጓዳችንን ስለምናውቀው ይበልጥ የሰመረ ውጤት ልናስመዘግብ እንችላለን።

በአሁኑ ወቅት ሁለት ሁኔታዎች ጐልተው ይታያሉ ፡

1. ወያኔ በሰላምም ሆነ በዓመጽ አብቅቶለታል። ስለ የማንኛውንም የፖለቲካ ድርጅት ጠንካራነት ለጊዜው እንተወውና ዛሬ ሕዝብ በራሱ ጠንክሯል። ወያኔ በተለይ ከግንቦቱ 97 የምርጫ ትርይት ወዲህ በየትኛውም ክልልና አካባቢ በሰላም ሊገዛ፡ ሊያስተዳድር ይሚያስችል ሁኔታ የለውም። ሕዝብና አገዛዙ ወያኔ ሊታረቁ በማይችሉበት ሁኔታ ተኮራርፈዋል። የተነቃነቀ ጥርስ መፍትዬው መነቀል ብቻ ነውና ወያኔም ተነቃንቋል። ወያኔ አንገቱ ላይ የተሸመቀቀለት ገመድ መጨረሻውን ያበስር ዘንድ የቆመበትን ወንበር የሚገፋለት ነው የጠፋው።
2. ወያኔ እንደ የካቲት 66 በሕዝብ ኃይል ግብታዊ ዓመጽ ቢወድቅ ቀጣዩ ማነው? ማነው ባለተራ? ማነው ሌላ ባለ 17 ዓመት? በከፍተኛ ሁኔታ ማሳሰብ ያለበት ጉዳይ ነው። ሕዝቡ ነው ሥልጣን የሚይዘው ወይስ ስለ ሕዝቡ አውቅልሃለው የሚሉ? ሕዝቡ ነው በሀገሩ ላይ ወሳኝ ወይስ አለንልህ ባዮች? ሕዝብ ነው ስለ መብቱ ተናጋሪ ወይስ ሌሎች?

ስለ ሀገር የለፈፈ፣ ባንዲራ ይዞ ያዙኝ ልቀቁኝ ያለ ሁሉ ለሕዝብ ሐሳቢ ነው ከሚል ድምዳሜ በመድረስ እንዳንሳሳት እሰጋለሁ። ይህ ቢሆን ከፋሽስቱ መንግስቱ ኃ/ማርያም በላይ አልነበረም። እናም ታሪክ በመደጋገም የታደለች ሀገር ናትና አሁንም ስለ ሀገር፣ ስለ ባንዲራ ብቻ እየተወራ፣ እየተጨኸ በዛ ሽፋን መሠረታዊ ጉዳዮችን የሚከረችም ሌላ ተረኛ እንዳይመጣ ልንጠነቀቅ ይገባናል። ለዚህም ነው የወያኔን የመውደቂያ አቅጣጫ ለማሳመርና ቀጣዩ የሀገራችን ዕድል ያሉትን የሰቆቃ፣ የመከራ፣ የስደት፣ የረሀብ፣ የበሽታ፣ የድንቁርና ወዘተ. ዘመናት ላለማየትና ለእኛ ሳይሆን ቢቻል ለልጆቻችን አለያም ለልጅ ልጆቻችን ብሩ ተስፋ እንድንጥል፣ ይህንን የግፍ አገዛዝ በነበር እንዲያስታውሱት፣ የሚገርም ነው ብለው እንዲያነቡት፣ ወይ ጉድ እንዲሉበት፣ እንዴት ይሆናል ብለው እንዲመራመሩበት ለማብቃት የቀድሞ የኢሕአፓ አባላት ያለንን የትግል ልምድ አሁንም ከኢሕአፓ ጋር በማድረግ ሀገራችንንና ሕዝባችንን ከተደቀነባቸው አደጋ ለማውጣት እንምከርበት። እንሰባሰብ።

ሀገሬን ሕዝቤን ካልን አሁን ወቅቱ ነው። ስለ ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ብዙ ባልልም በአጠቃላይ ለአለፉት 16 ዓመታት ብቅ ካሉት የፓለቲካ ድርጅቶች ውስጥ አሁንም የትኛውም ድርጅት የሕዝቡን ትግል ሊመራ እንዳልቻለ እናያለን። ሕዝቡ ከድርጅቶቹ ቀድሞ ሄዷል። ሕዝቡ እጅግ ነቅቷል። ይህ ሕዝብ ከወያኔ ጋር እያደረገ ያለውን የሞት የሽረት ፍልሚያ በመገንዘብ ትግሉን በሚያመረቃ ሁኔታ ለድል ለማብቃት የገባነውን ቃል ኪዳን እናድስ። አለብን አደራ።

ዛሬ የኢትዮጵያን ሕዝብ አታልላለሁ የሚሉ ቢኖሩ ያለምንም ጥርጥር ከራሳቸው ሌላ የሚያታልሉት አለመኖሩን ሊገነዘቡ ይገባል። ሕዝብ አልገዛም በቃኝ ሲል፣ ያለጥርጥር ቁርጠኝነቱ ሲታወቅ አይደለም ታጋይ ለመሆን መነሳሳት። ደርግን መውደቂያው ላይ አልነበረም ለመዝለፍ መነሳሳት። ወያኔ ሲንገዳገድ አይደለም አለሁ ማለት። የቤተ መንግሥት በር ሲከፈት አይደለም ማን ሞኝ አለ ማለት። ወያኔን ለመጣል መስዋዕትነት እየከፈለ ያለውን ሕዝብና ልጆቹን አያገባኝም እያሉ አይደለም መሞዳሞድ። አሁንም ዲሞክራሲ፣ አሁንም ሸንጎ፣ አሁንም ምርጫ፣ አሁንም ሕገ መንግሥት እያሉ ደንቁረው ሕዝብ ሊያደነቁሩ የተነሱ አሉ ባይባሉም ሊኖሩ ይችላሉ ብለን ታማኝነታችንን፣ ቁርጠኛነታችንን፣ ሀገርና ሕዝብ ወዳድነታችንን ለዚህ ዳግም ጥሪ መልስ በመስጠት የበኩላችንን እናበርክት።

ለማጠቃለል አሁንም ኢትዮጵያ ሀገራችን ያለችበትን አስከፊ ሁኔታና ሕዝባችን ከተደገሰለት አደጋ ለማዳን በአለን አቅምና ችሎታ ቢቻል ድርጅቱን እንደገና በመቀላቀል ማየት ለምንፈልገው ራዕይ ስኬታማነት የትግል አርማችንን እናንሳ። ለተደረገው የትግል ጥሪ አዎንታዊ ምላሽ በመስጠት ላልተመለሰውና መፍትሔ ላላገኘው የሀገራችን ችግር አሁንም ኢሕአፓን ተቀላቅለን የተሰዉ ጓዶቻችንን አደራ እንወጣ ዘንድ እኔም ከጠሪው ወገናችሁ ከኢሕአፓ መልእክተ ተጠሪነቴን አቀርብኩላችሁ። ባንድ ቃል ወደ ቤታችሁ ትመለሱ ዘንድ አክብሮታዊ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ። አመሰግናለሁ።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!